በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 እና 8

1. ከሚከተሉት ውስጥ ማርያም እንተ እፍረት ካደረገችው ነገር የምንማረው የቱን ነው?
ሀ) በዕንባዋ የጌታችንን እግር ማጠቧ ንስሐን ያስተምረናል
ለ) በራስ ጸጉሯ የጌታችንን እግር ማበሷ ትሕትናን ያስተምረናል
ሐ) የጌታችንን እግር መሳሟ ፍቅርን ያስተምረናል
መ) ዋጋው ውድ የሆነ ሽቱ የጌታችንን እግር መቀባቷ አክብሮን ያስተምረናል
ሠ) ሁሉም መልስ ናቸው

2. ."....ብዙዎች ሌላዎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር።" የተሰመረበት ቃል ፍቺ የሆነው የቱ ነው?
ሀ.በህዋሳታቸው ንጽሕናን ይዘው ያገለግሉት ነበር
ለ.ለጌታ መብልና መጠጥ በማቅረብ ያገለግሉ ነበር
ሐ.አስራት በኩራታቸውን እያወጡ ይሰጡ ነበር
መ.ሁሉም

3. ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በናይን ያደረገው ተአምር የቱን ነው?
ሀ) የኃጢአተኛዋን በደል ይቅር ማለት
ለ) የመበለቷን ልጅ ከሞት ማስነሳት
ሐ) የመቶ አለቃውን አገልጋይ መፈወስ
መ) መጥምቁ ዮሐንስን ደቀመዛሙርቱን ልኮ ከእስር ማስፈታት

4. "...ርስ በርሳቸውም፦እንዲህ ነፋሳትንና ውሃን እንኳ የሚያዝ ለርሱም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው አሉ።" ይህንን የተናገሩት እነማን ናቸው?
ሀ.ረበናት አይሁድ
ለ.ሐዋርያት
ሐ.ሕዝቡ
መ.ፈሪሳውያን

5. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ጌታችን የመበለቲቱን ልጅ በምን ሁኔታ ላይ እያለ አዳነው?
ሀ)ታሞ በአልጋ ላይ ሳለ
ለ)ሞቶ በእናቱ እቅፍ ሳለ
ሐ)ሞቶ ሬሳውን ተሸክመው ሲሄዱ
መ)ሁሉም

6. ጌታችን ወደ ኢያኢሮስ ቤት ሲገባ አብረውት እንዲገቡ የፈቀደው ለማን ነበር?

ሀ.ለሐዋርያቱ
ለ.ለልጅቱ እናት እና አባት
ሐ.ያዕቆብ, ዮሐንስ እና ጴጥሮስ
መ.ለ እና ሐ

7. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ጌታችን ተዘዋውሮ ሲያስተምር አብረውት ከነበሩት ውስጥ የማይጠቀሱት እነማን ናቸው?
ሀ)12ቱ ሐዋርያት
ለ)መግደላዊት ማርያም ሶስና ዮሐና
ሐ)መጥመቁ ዮሐንስ
መ)ሁሉም

8. ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌጌዎን የተባሉትን አጋንንት ያወጣቸው በየት ነው?
ሀ)ጌርጌሴኖን ለ)ናይን ሐ)ናዝሬት መ)ሁሉም

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 እና 8 በአጠቃላይ ስንት ሰው ከሞት አስነሳ?
ሀ) አንድ ለ)ሁለት ሐ)ሦስት መ)አራት

10. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ልብስ በመዳሰስ የዳነችው ሴት ስንት ዓመት ደም ይፈሳት ነበር?
ሀ)9 ለ)10 ሐ)11 መ)12

11. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ሐዋርያት የነበሩበት መርከብ በአውሎ ንፋስ ሲናወጽ ጌታ በየት ነበረ?
ሀ) በተራራ ሲጸልይ ቆይቶ
ለ) ሕዝቡን አሰናብቶ እየተመለሰ
ሐ) ተኝቶ
መ) ሀ እና ለ

12. "በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር " ምሳሌነቱ ለምንድን ነው?
ሀ) ሰምቶ ለጊዜው ደስ ብሎት የሚቀበል፤ መከራና ስደት ሲሆን ፈጥኖ የሚክድ
ለ) ቃሉን ሰምቶ ያላስተዋለ፣ ዲያብሎስ መጥቶ በልቡናው የተዘራውን የሚያጠፋበት
ሐ) ሰምቶ፣ አስተውሎ የሚሰራ
መ) ቃሉን ሰምቶ የዚህ አለም ሃሳብ እና የሃብት ማታለል አንቆት ያለ ፍሬ የሚቀር

13. ዘር እና ዘሪ ተብለው የተመሰሉት ምንድን እና ማን ናቸው?

ሀ) ቁርባን እና ሐዋርያት

ለ) ወንጌል እና ጌታችን

ሐ) ዕጣን እና መላእክት

መ) ብሉይ ኪዳን እና ሐዋርያት

14. በጭንጫ ላይ የወደቀው ዘር ትርጉም ምንድን ነው?

ሀ) በመጀመርያ ቃሉን በደስታ የሚቀበለው ነገር ግን በቃሉ ምክንያት መከራ ሲመጣ መቋቋም ሚያቅተው

ለ) ክፉ ዲያቢሎስ የተማረውን ቃል ሳያድግ የሚወስድበት

ሐ) ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል

መ) መልስ አልተሰጠም

15. በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር ምሳሌ ላይ ወፎች ተብለው የተጠቀሱት ምንድን ናቸው?

ሀ) ቅዱሳን መላእክት

ለ) ክፉ(አጋንንት)

ሐ)ርግቦች

መ)ሁሉም

16. ዘሪ ዘሩን ከዘራባቸው ቦታዎች ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) መንገድ ላይ

ለ)ጭንጫ ላይ

ሐ)ወፎች ጎጆ ውስጥ

መ)እሾህ መካከል

17. ከሴቶች ከሚወለዱ ወገን የሚበልጠው የለም የተባለለት ማን ነው?

ሀ) ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ

ለ) መጥምቁ ዮሐንስ

ሐ) ጴጥሮስ

መ) ኤልያስ

18. አስቀድሞ የመጥምቁ ዮሐንስ፣ ኋላም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር የነበረው የቱ ነው?

ሀ) ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ

ለ) እንድርያስ

ሐ) ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ

መ) ለ እና ሐ

19. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 "በእስራኤልስ እንኳ እንዲህ ያለ እምነት አላገኘሁም" የተባለለት ማን ነው?

ሀ) ጴጥሮስ

ለ) ሎሌው የታመመበት መስፍን

ሐ) የሐንስ

መ) ይሁዳ

20. ጌታችን በገሊላ አውራጃዎች እየዞረ ሲያስተምር ይከተሉት ከነበሩት ሴቶች ውስጥ የማትካተተው የትኛዋ ናት?

ሀ) መግደላዊት ማርያም ለ) የሐና ሐ) ሶስና መ) ማርታ ሠ) ሀ እና መ